## በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

# የቱሪዝም ዘርፍ
# የዕውቅና እና የሽልማት አሰጣጥ
# መመሪያ ቁጥር 476/2013

ሰኔ 2008

# የቱሪዝም ዘርፍ

# የዕውቅና እና የሽልማት አሰጣጥ

# መመሪያ ቁጥር 476/2013

ምርቶቻቸውንና አገልግሎታቸውን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለቱሪስቶችና ለሌሎች ተጠቃሚዎች የሚያቀርቡ የቱሪዝም አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችና ተቋማት በተናጠልና በጋራ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ፤ ለቱሪዝም ልማት ዕድገት መፋጠንና ሀገሪቱ ከዘርፉ ለምታገኘው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ መዳበር የሚጫወቱት ሚና የላቀ በመሆኑ፤

የዘርፉ ባለድርሻ አካላት እና አጋሮች በቱሪዝም ሴክተር የሰው ሀይል ልማትና የአቅም ግንባታ፣ በባህላዊና ተፈጥሯዊ የቅርስ ሀብቶችና የቱሪስት መዳረሻዎች ጥበቃና ልማት፣ በአገልግሎት አሰጣጥ፣ በመልካም ገጽታ ግንባታ፣ የቱሪዝም መስህቦች በማስተዋወቅ እና ከዘርፉ ልማት የሕብረተሰቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በሚከናወኑ ተግባራት ላይ በግልም ሆነ በመቀናጀት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረጉ በመሆኑ፤

የዘርፉ ባለድርሻዎችና አጋሮች የሚያበረክቱትን ዘርፈ ብዙ አስተዋፅዖ በዘላቂነት ለማስቀጠል፤ በየወቅቱ ለሴክተሩ ስኬታማ መሆን የላቀ አስተዋፅዖ ለሚያበረክቱ፣ ልዩ ሚና ለሚጫወቱና በሞዴልነት ለሚታዩ ሁሉ አቅምና ሁኔታ በፈቀደ መጠን ለፈፀሟቸው ተግባራት ዕውቅና እና ሽልማት መስጠት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በዘርፉ የሚገኙ ባለድርሻዎችን በየሥራዎቻቸው አርአያነታቸውን ለይቶ ሀገራዊ ዕውቅናና ማበረታቻ በመስጠት፤ ለተሻለ ሥራና መልካም ውጤት በማነሳሳት በጥረት ላይ የተመሠረተ የውድድር ስሜት መፍጠር ተገቢ በመሆኑ፤

የዕውቅና እና የሽልማት አሰጣጥ ሥርዓት የታቀደ የተጠና፣ ወጥ፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት ባለው መልኩ መከናወን ያለበት በመሆኑ፤

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀፅ 35 የተሠጡትን ተግባርና ኃላፊነቶች በአግባቡ ለመወጣት ይህንን መመሪያ አወጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ
# ጠቅላላ

## 1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "የቱሪዝም ዘርፍ የዕውቅና እና የሽልማት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 476/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) **"መመሪያ"** ማለት የቱሪዝም ዘርፍ የዕውቅና እና የሽልማት አሰጣጥ መመሪያ ነው፡፡
2) **"ዘርፍ"** ማለት በቱሪዝም ተግባር የተሰማሩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት፣ በቱሪስት እሴት ሰንሰለት በተለያዩ የንግድ ሥራዎችና ሙያዎች የሚንቀሳቀሱ አገልግሎት ሰጪዎች፣ የሴክተሩ ተዋንያን፣ የዘርፉ ባለድርሻዎች እና አጋር አካላትን የሚያካትት ነው፡፡
3) **"ዕውቅና"** ማለት ለቱሪዝም ዘርፍ ልማትና ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽዖ ላደረጉ ዜጎች ወይም አካላት ላከናወኑት ልዩና አርአያነት ያለው ተግባራቸው በመመሪያው መሠረት በሚኒስቴሩ በይፋ እንዲታወቁ የሚደረጉበት ሂደት ነው፡፡
4) **"ሽልማት"** ማለት ለቱሪዝም ዘርፍ ልማትና ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽዖ በማበርከታቸው በመመሪያው መሠረት ዕውቅና ላገኙ ወይም በውድድር አሸናፊ ለሆኑ በገንዘብ ወይም በዕቃ ወይም በአገልግሎት መልክ የሚሰጥ ስጦታ ነው፡፡
5) **"ማህበራት"** ማለት በቱሪዝም የተለያዩ የንግድና የሙያ መስኮች ተደራጅተው የሚንቀሳቀሱ ማህበራት ናቸው፡፡
6) **"ኮሚቴ"** ማለት የዕውቅና እና የሽልማት ሥርዓትን በዋናነት እንዲመራ የሚቋቋመው ዓብይ ኮሚቴ ነው፡፡
7) **"ክልል"** ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 47(1) የተመለከተውን ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ መስተዳድሮችንም ይጨምራል፡፡
8) **"ቢሮ"** ማለት የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ነው፡፡
9) **"ሚኒስቴር"** ማለት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ነው፡፡
10) ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

## 3. ዓላማ

የዕውቅና እና ሽልማት ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1) ለቱሪዝም ልማትና ዕድገት ከፍተኛ አስተዋፅዖ ላደረጉ የዘርፉ ባለድርሻዎች ለፈጸሙት አርአያነት ያለው ልዩ ተግባር ዕውቅና ለመስጠትና ማበረታታት፤
2) በዘርፉ በተሰማሩ ባለድርሻዎች መካከል ጤናማ የውድድር ስሜት እንዲፈጠርና የእርስ በርስ የልምድና የተሞክሮ ልውውጥ እንዲደረግ ማበረታታት፤
3) በዘርፉ የሚንቀሳቀሱ ባለድርሻዎች በየጊዜው ለአዲስ ፈጠራ፣ ጥናትና ምርምር እና ስኬታማ አፈጻጸም እንዲነሳሱ ማድረግ፤
4) በዘርፉ የተለያዩ የኢንቨስትመንት ዕድሎች እንዲፈጠሩ ለማበረታታት እና ባለሀብቶችን መሳብ፤
5) ለቱሪዝም ልማት ዕድገት መፋጠን የሚካሄዱ በላቀ ደረጃ የሚፈረጁ የሥራ ውጤቶችና ስኬቶችን በማስተዋወቅ ለሀገር ገጽታ ግንባታ የበኩላቸውን በጎ አስተዋጾኦ እንዲያደርጉ ማበረታታት፤
6) በቱሪዝም ዘርፍ የተለያዩ የሥራ መስኮች በሚመዘገብ የላቀ የሥራ ውጤት ምክንያት በሚሰጠው ዕውቅና እና ሽልማት የተቋሙን በጎ ገጽታና የሴክተሩን ስኬታማ ተግባራት በየጊዜው ማስተዋወቅ፡፡

## 4. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በአገር አቀፍ ደረጃ በሚያዘጋጀው የእውቅና እና የሽልማት አሠጣጥ ሥነ-ሥርዓት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለዕውቅና እና ሽልማት

### 5. የዕውቅና እና የሽልማቱ መርሆዎች

1) ለዕውቅና እና ሽልማቱ የሚቀርቡ ባለድርሻዎችን በመለየት ፣ በማወዳደርና በመምረጥ ሂደት ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው አሰራርና አካሄድ መኖሩን ማረጋገጥ፤
2) በዕውቅናና በሽልማቱ አጠቃላይ ሂደት የሚመለከታቸውን የዘርፉን ባለድርሻ አካላት ተሳትፎን ማረጋገጥ፤
3) ለዕውቅና እና ለሽልማት የሚበቁ ባለድርሻዎች ለሀገር፣ ለሕብረተሰቡና ለዘርፉ ውጤታማ እና ስኬታማ ተግባር ማበርከታቸውን ማረጋገጥ፤
4) ለዕውቅና እና ለሽልማት የሚመረጡ አካላት ያበረከቱት ልዩ አስተዋጽዖ ለሌሎች በአርአያነት ሊታይ የሚችል መሆኑን ማረጋገጥ፤
5) የዕውቅና እና የሽልማት ሥርዓት የመዘርጋቱ ዓላማና አፈጻጸሙ በዘርፉ ተዋንያንና ባለድርሻ አካላት መካከል ግንዛቤ መፈጠሩን ማረጋገጥ፤
6) ለሽልማት የሚቀርቡ ሥራዎች የሀገራችንን ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብዝሃ የቱሪዝም መስህቦችን ለመጠበቅ፣ ለማልማት ለማስተዋወቅና ለዘርፉ የተሻለ ተጠቃሚነትን ለመፍጠር የሚያስችል አቅም ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ፤

### 6. ስለተሸላሚዎች አግባብነት

1) ማንኛውም በዘርፉ የላቀ አስተዋጽዖ ያበረከተ እና የዕውቅና እና የሽልማት መስፈርቱን የሚያሟላ ሰው ወይም ድርጅት ይሸለማል፡፡

2) ማንኛውም የቱሪዝም ዘርፍ ተሸላሚ ቀደም ብሎ በተሸለመበት ተግባር በድጋሚ ሊሸለም የሚችለው ከዚህ ቀደም ባከናወነው ሥራ ላይ ተጨማሪ የማስፋፊያ ወይም የማበልፀጊያ ወይም የማሻሻያ ሥራ አክሎበት የተገኘ ከሆነ ነው፡፡

## 7. ዕውቅና እና ሽልማት የሚሰጥባቸው የቱሪዝም ዘርፍ የሥራና የሙያ መስኮች

**1) የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች**

ሀ. ሆቴሎች፣ ሎጆች፣ ሪዞርቶች፣ ሞቴሎች፣ ፔኒሲዮኖች፣የእንግዳ ማረፊያዎች፤

ለ. ሬስቶራንቶች ፣ የምግብና መጠጥ አገልግሎት ሰጪዎች፤

ሐ. ባህላዊ ምግብ ቤቶች፣ ባህላዊ መዝናኛ ቦታዎች፤

መ. አስጎብኚ ድርጅቶች፤

ሠ. ግለሰብ አስጎብኚዎች ( ጋይዶች)፤

ረ. ህጋዊ አሳዳኝ ድርጅቶች እና ግለሰብ ባለሙያ አሳዳኞች፤

ሰ. የጉዞ ወኪሎች፤

ሸ. ሙዚየሞች፤

ቀ. በቱሪዝም ዘርፍ ልዩ የኩነት አስተባባሪዎች፤

በ. ባህላዊ የስጦታ ዕቃዎች፣ የዕደ ጥበብ ውጤቶች፣ የገፀ-በረከት ዕቃዎች አምራቾች፤

**2) የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች**

ሀ. አየር መንገዶች፤

ለ. የቱሪስት ታክሲ አገልግሎት ሰጪዎች፤

ሐ. መኪና አከራዮች፤

መ. አገር አቋራጭ አውቶብሶች፤

**3) የማሰልጠኛ ተቋማት፣ የማማከር አገልግሎቶች**

ሀ. በቱሪዝም ዘርፍ የተሰማሩ ማሰልጠኛ ተቋማት፤

ለ. በቱሪዝም ዘርፍ የማማከር አገልግሎት የተሰማሩ፤

ሐ. በቱሪዝም ዘርፍ በማስተዋወቅ ተግባር የተሰማሩ አካላት፤

**4) ሌሎች የዘርፉ ባለድርሻ አካላት እና አጋር ድርጅቶች**

ሀ. የክልልና ከተማ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች፤

ለ. በዘርፉ የሚንቀሳቀሱ ማህበራት፤

ሐ. በቱሪዝም ዘርፍ የሚንቀሳቀሱ የመገናኛ ብዙሀን አካላት እና የሚዲያ ባለሙያዎች፤

መ. የሀገራችንን እንወቅ ክበባት፤

ሠ. በብሔራዊ ፓርኮች እና በዱር እንስሳት ልማት የተሠማሩ አካላትና ግለሰቦች፤

ረ. በተፈጥሮ አካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ሥራዎች የተሠማሩ አካላትና ግለሰቦች፤

ሰ. በመስህቦች ልማት እና እንክብካቤ የተሰማሩ አካላትና ግለሰቦች፤

ሸ. በቅርስ እንክብካቤ የተሰማሩ አካላትና ግለሰቦች፤

ቀ. በአዳዲስ የቱሪዝም ምርቶች ፈጠራ የተሰማሩ አካላትና ግለሰቦች፤

በ. የፌዴራልና የክልል መንግስታት መሥሪያ ቤቶች፤

ተ. በውጭ አገር የኢትዮጵያ ቆንስላ ጽሕፈት ቤቶችና ኤምባሲዎች፤

ቸ. መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ተቋማት፤

ኀ. በዘርፉ በተለያዩ የሥራ መስኮች ልዩ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን የሚያከናወኑ ግለሰቦች፤

## 8. የዕውቅና እና የሽልማት ጥቅል መመዘኛዎች

1) ከአገልግሎትና ከሽያጭ የተገኘ ገቢ በብር፤
2) ከውጭ ምንዛሪ የተገኘ ገቢ፤
3) የቱሪስቶች፣ የተስተናገዱ ጎብኚዎች ፣ ተገልጋዮች ወይም ደንበኞች ብዛት፤
4) የተፈጠረ የሥራ ዕድል ብዛት፤
5) በተሰማሩበት የሥራ መስክ ከፍተኛ ጥራት ያለው አገልግሎት ከመስጠት አንፃር፤
6) የመዳረሻ አካባቢ ሕብረተሰብን ተጠቃሚ ከማድረግ አኳያ የተከናወኑ ተግባራት፣
7) የሴቶችና ወጣቶች ተጠቃሚነትና ተሳታፊነትን ከማሳደግ አንፃር የተከናወኑ ተግባራት፤
8) በዘርፉ በሚደረገው የልማት እንቅስቃሴ የአካል ጉዳተኞችን ሁኔታ ለማካተት የተከናወኑ ልዩ ተግባራት

9) በውጭና በሀገር ውስጥ በሚደረጉ የንግድ ትርዒቶችና ኤግዚቢሽኖች የተደረጉ ተሳትፎዎች፤

10) በግንባታ፣ በአደረጃጀትና በአገልግሎት አሰጣጥ፤ ባህላዊ፣ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ ሀብቶችን የመጠቀምና የማስተዋወቅ ጥረት፤

11) ከግንባታ እስከ አገልግሎት አሰጣጥ ለማህበረሰብ ተኮር ኤኮ ቱሪዝምና ለአካባቢ ጥበቃ የተሰጠው ግምት፤

12) በቱሪስት መዳረሻዎችና መስህቦች የአካባቢ ልማትን ለማፋጠን የተከናወኑ ሥራዎች፤

13) ለሀገር ገጽታ ግንባታ የተከናወኑ ተግባራት፤

14) የሰው ሀብት ልማትና የማስፈጸም አቅም ግንባታ እንዲሁም በዘርፉ የሰለጠነ ባለሙያ በማፍራትና ግንዛቤ በመፍጠር የተከናወኑ ተግባራት፤

15) በዘርፉ የተከናወኑ የጥናትና የምርምር የሥራ ውጤቶች፤

16) በተሰማሩበት የሙያና የሥራ መስክ በሥነ-ምግባር፣ በደንበኛ አያያዝ፣ በንጽሕና አጠባበቅ እና በአገልግሎት አሰጣጥ ለሌሎች አርአያነት ያለው፣ በሞዴልነት ሊወሰድ የሚችል የላቀ የሥራ አፈጻጸም ውጤት ያስመዘገቡ፤

17) የሀገር ውስጥ ምርቶችና አገልግሎቶችን የመጠቀም ሁኔታ፤

18) አማራጭ ታዳሽ የሀይል ምንጮችን በመጠቀም ረገድ የተወሰደ እርምጃ፤

19) በአገልግሎት አሰጣጥ የታየ ተጨባጭ የላቀ አስተዋፅዖ፤

20) የሀገር ውስጥ ቱሪዝምን ለማስፋፋት የተካሄዱ ጉብኝቶችና የተከናወኑ ተግባራት፤

21) ማህበራትን ከማጠናከር የአባላትንም ቁጥርና ተሳትፎ ከማሳደግ አንጻር የተከናወኑ ሥራዎች፤

22) ከተገልጋዮች ጋር ከጊዜ፣ ከአሠራር፣ ከዖታ፣ ከእድሜና ከአካል ጉዳተኝነት አንፃር ያለው ተደራሽነት፤

23) አሰራርን በዘመናዊ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ከመደገፍ፣ ተቀባይነትና ግልጽነት ባለው የመረጃ ሥርዓት ከመጠቀም አንጻር የታዩ ተጨባጭ ሥራዎች፤

24) ለቱሪዝም ልማትና ዕድገት የመሠረተ-ልማት አውታሮች ከመገንባትና ከማስፋፋት አንፃር የተከናወኑ ሥራዎች፡፡

## 9. የዕውቅና እና የሽልማት አሰጣጥ ሥርዓት

1) የዕውቅና እና የሽልማት ዝግጅት በዓመት አንድ ጊዜ ይካሄዳል፡፡

2) የዕውቅና እና የሽልማት አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት እራሱን ችሎ በሚካሄድ ዝግጅት የሚከናወን ሆኖ፣ በሚኒስቴሩ ሲታመንበት ከሎሎች ዝግጅቶች ጋር በማቀናጀት ማካሄድ ይቻላል፡፡

3) አንድ ሥራ ለሽልማት የሚበቃው ለየዘርፉ የተዘረዘሩትን የመመዘኛ መስፈርቶች ሲያሟላ እና በኮሚቴው የነጥብ አሰጣጥ ከሌሎች የላቀ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ይሆናል፡፡

## 10. ስለዕውቅና እና ሽልማትይዘት

1) ዕውቅና ለሚያገኘው አካል ስለሚሰጠው ማስረጃ ይዘት ኮሚቴው የሚያቀርበው የውሳኔ ሀሳብ በሚኒስቴሩ ሲጸድቅ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
2) ስለሚሰጠው የሽልማት ዓይነት፣ ይዘትና ተመን ኮሚቴው የሚያቀርበው የውሳኔ ሀሳብ በሚኒስቴሩ ሲጸድቅ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሶስት
# ስለዕውቅና እና ሽልማት አሰጣጥ ኮሚቴ

## 11. መቋቋም

1) ሚኒስቴሩ የቱሪዝም ዘርፍ የዕውቅና እና ሽልማት ሥርዓትን በዋናነት የሚመራ ዓብይ ኮሚቴ ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በማዋቀር ያቋቁማል፤ የአባላቱም ቁጥር እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል፡፡
2) ሚኒስቴሩ የኮሚቴውን ሰብሰቢ ይሰይማል፡፡

## 12. የኮሚቴው ስብሰባ

1) ኮሚቴው የራሱን የስብሰባ ጊዜና ቦታ ይወስናል፡፡
2) ከኮሚቴው አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡
3) የኮሚቴው ውሳኔ በአብላጫ ድምፅ ይወሰናል፤ ድምፁ ለሁለት እኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፡፡
4) ኮሚቴው የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 13. የኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት

ኮሚቴው የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

1) ኮሚቴው የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት እንዲያስችለው እንደአስፈላጊነቱ ንዑሳን ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፡፡

2) የዓመቱን የዕውቅና እና ሽልማት አሰጣጥ አጠቃላይ መርሀ-ግብር በማውጣት ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
3) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 ከተዘረዘሩት ጥቅልና ጠቋሚ የማወዳደርያ መመዘኛዎች አንዱን ወይም የተወሰኑትን በመውሰድ እንደ ዘርፉ የሥራና የሙያ መስኮች እና እንደ ክልሎች ተጨባጭ ሁኔታ ዝርዝር መስፈርቶችን በማዘጋጀት ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
4) ዕጩዎችን ለመምረጥ የሚያስችለውን መረጃ ያሰባስባል፣ ያደራጃል ፡፡
5) ለሥራው ስኬታማነት ከሴክተሩ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፡፡
6) ለሽልማት ግዢ፣ ለዕውቅና እና ለሽልማቱ ዝግጅት ሥነ-ሥርዓት የሚያስፈልገው ወጪ በሚኒስቴሩ በተያዘው በጀት ወይም በባለድርሻ አካላት ድጋፍ ወይም በስፖንሰሮች ሊሸፈን እንደሚችል ያረጋግጣል፡፡
7) ለዕውቅና እና ለሽልማት አመራረጥ ያከናወናቸውን የአፈጻጸም ተግባራት እና የአሸናፊዎች ዝርዝር ሪፖርት ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡
8) ለአሸናፊዎች የሚሰጠውን የዕውቅና እና የሽልማት ዓይነት በመለየት የውሳኔ ሀሳብ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
9) የዕውቅና እና የሽልማት አሰጣጥ አጠቃላይ አፈጻጸምን በመገምገም ሪፖርት ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

## 14 የሚኒስቴሩ ተግባርና ኃላፊነት

ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

1) ዓብይ ኮሚቴውን ያቋቁማል፣ ይደግፋል፣ በየወቅቱ አፈጻጸሙን ይገመግማል፣
2) በበጀት ዓመቱ ዕውቅና እና ሽልማት የሚሰጥባቸውን የዘርፉን የሥራና የሙያ መስኮች ይወስናል፣
3) ኮሚቴው ያዘጋጀውን የዓመቱን የዕውቅና እና የሽልማት መርሀ-ግብር እና ዝርዝር መስፈርቶች ያጸድቃል
4) ለክልል ቢሮዎች የዓመቱ የዕውቅና እና የሽልማት መርሀ-ግብር፣ የዘርፉን የሥራና የሙያ መስኮች ኮሚቴው ከሚያወጣው ዝርዝር መስፈርቶች ጋር ያሳውቃል፣
5) የክልል ቢሮዎች በመመሪያውና በዓመቱ መርሀ-ግብር መሰረት ለዕውቅና እና ለሽልማት የሚቀርቡ ተወዳዳሪዎችን እንዲያሳውቁ በጽሁፍ ጥሪ ያስተላልፋል፣

6) ከክልል ቢሮዎች የሚመጡ የዕውቅና እና የሽልማት ውድድርን የሚመለከቱ መረጃዎችን ለኮሚቴው ያሳውቃል፣
7) ለኮሚቴው ሥራ መቃናት አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣
8) የዕውቅና እና የሽልማት ስነ-ሥርዓትን በበላይነት ይመራል፣
9) ለሽልማት አሰጣጥ የሚያስፈልገውን በጀት ይመድባል፣
10) ከክልል ቢሮዎችና ከኮሚቴው ጋር በጥምረት ይሠራል፣
11) ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የፌዴራል መሥሪያ ቤቶች ትብብርና ድጋፍ ይጠይቃል
12) የተሸላሚዎችን መረጃ ያደራጃል፣ ለሚመለከታቸው ያሳውቃል፣
13) የዕውቅና እና የሽልማቱ ፕሮግራም የመገናኛ ብዙኀን ሽፋን እንዲያገኝ ያደርጋል፣
14) የሚነሱ ቅሬታዎችን ተቀብሎ ተገቢውን ምላሽ እንዲሰጥ ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው ይመራል፡፡

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ

## 15. የቅሬታ አቀራረብ

1) በእውቅና እና በሽልማት አሰጣጥ ሂደት ላይ ቅሬታ ያለው አካል ዝግጅቱ በተካሄደ በ10 (አስር) ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለቱሪዝም ዘርፍ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በጽሑፍ ማቅረብ ይችላል፡፡
2) ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው በዕውቅና እና በሽልማት አሰጣጥ ሂደት ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በመቀበል በ5 (አምስት) የሥራ ቀናት ውስጥ ተገቢውን ምላሽ ይሰጣል፡፡
3) የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ውሳኔው በተገለፀለት በ5 (አምስት) የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ አመራር ማቅረብ ይችላል፡፡
4) የበላይ አመራሩ ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

## 16. መመሪያውን ስለማሻሻል

ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

## 17. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከፀደቀበት ሰኔ 2008 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡